# የደን ልማት፣ ጥበቃና
# አጠቃቀም ፖሊሲና ስትራቴጂ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር

# ማ ው ጫ


**ርዕስ** **ገጽ**

መግቢያ... ... ...... ... ... ... ... ... ... ... ... . ... ... ... ... ... ... ... ...... ... ... ..

የፖሊሲው ዓላማዎች ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ......

አጠቃላይ ዓላማ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... .. ... ... ... ... ... ... ... ... ...

ዝርዝር ዓላማዎች... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... .

ፖሊሲና ስትራቴጂ.... ... ... ... ... ... ... ... ... ... ... .. ... ... ... ... ... ... ... ... ...

1. የግል ደን ልማትና ጥበቃ እንዲስፋፋ ስለማድረግ. ......... ... ... ... ... ... ..
2. የደን ልማት ቴክኖሎጂ ስለማስፋፋት... ... ... ... ... ... . ... ... ... .. ... ...
3. የደን ገበያ ልማት ስለማስፋፋት... ... ... ... ... ... ... ... ... ...... ... ... ... ..
4. የመንግሥት ደን አስተዳደርና ማኔጅመንት... ... ... ... ... ... ... ... ... .......
5. የደን ሀብትን ከልዩ ልዩ ጥፋቶች መከላከል.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ....
6. በደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ስለመዘርጋት...

## መግቢያ

ሀገራችን ለደን ሀብት ልማት ምቹ ሁኔታዎች ቢኖሯትም ለረጅም ጊዜ በቆየው የደን ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ኋላቀርነት የተነሳ ከንዑስ ዘርፉ የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ተፈጥሮአዊ ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች። ለዚህ ዝቅተኛ አስተዋፅኦ ካበረከቱት መንስኤዎች ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመጣው የሕዝብ ብዛት የተነሳ ለእርሻ መሬት ደንን መመንጠር፣ የማገዶና የኮንስትራክሽን ፍጆታ መጠን መጨመር፣ በሕገ-ወጥ መንገድ በደን ውስጥ መስፈርና ሕገ-ወጥ የደን ቆረጣና ህገወጥ ንግድ መስፋፋት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። በመሆኑም የደን ሀብታችን መመናመን የብዝሀ ሕይወት መቀነስን፣ የአፈር መሸርሸርን፣ የመሬት መናድን/መንሸራተትን፣ የመሬት መራቆትንና፣ የበረሃማነት መስፋፋትን፣ የድርቅና ረሀብ ድግግሞሽን አስከትሏል። ስለዚህ የተገለጹትን ችግሮች ለመፍታትና የደን ሀብታችንን፣ በዘላቂነት በማልማትና በመጠበቅ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ ለማበርከትና የአካባቢ ተፈጥሮአዊ ሚዛንን ለመጠበቅ የብዝሀ ሕይወት ሀብታችንን ለመንከባከብና ለማበልፀግ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ ዘላቂ ልማትና እድገት ለማምጣት የሚያስችል የደን ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

# የፖሊሲው ዓላማዎች

## አጠቃላይ ዓላማ

የፖሊሲው ዋና ዓላማ የሀገራችንን የደን ሀብት በአግባቡ በመጠበቅ፣ በማልማትና የሕብረተሰቡን የደን ዉጤቶች ፍላጎት ማሟላትና ደን ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ማድረግ ነው፡፡

## ዝርዝር ዓላማዎች

1/ በደን ሀብት ልማት ለሚሰማሩ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች፣ ባለሀብቶችና ተቋማት ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት የደን ልማቱን በዘላቂነት እንዲያስፋፉ ለማበረታታት፣

2/ ለደንና ለደን ሀብት ልማት ተስማሚ በሆኑ አካባቢዎች የደን ሀብት ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት በማሻሻልና በማሳደግ የሕብረተሰቡን የደንና የደን ውጤቶች ፍላጎት በሚገባ ለማሟላት፣

3/ ለሀገራችን ተስማሚ የሆኑና ልዩ ልዩ ጠቀሜታ ያላቸውን የደን ዕፅዋት በመምረጥ፣ በማሻሻል፣ በማባዛትና በማሰራጨት የደን ሀብት ልማት በዘላቂነት እንዲስፋፋ በማድረግ ለምግብ ዋስትናና ለኢንዱስትሪ የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ለማሳደግ፣

4/ የደን ሀብትን ከማናቸውም ጥፋቶች በመከላከል፣ በመንከባከብና በማልማት ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጥቅም በዘላቂነት እንዲሰጥ መሰረት ለመጣል፣

---

5/ የሀገራችንን የደን ሀብት በሚገባ በመንከባከብና በማልማት ከባቢያዊ
የተፈጥሮ ሚዛን በዘላቂነት ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግናቸው፣

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን አላማዎች በማገናዘብ፣ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ለተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች በተለይም ለመሬት አጠቃቀም ከወጡ ፖሊሲዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የደን ሀብት ለመጠበቅና ለማልማት እንዲሁም ዘለቄታ ባለው መንገድ በጥቅም ላይ ለማዋል ይቻል ዘንድ ከዚህ በታች የቀረበው የደን ፖሊሲና ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል።

## ፖሊሲና ስትራቴጂ

## 1. የግል ደን ልማትና ጥበቃ እንዲስፋፉ ስለማድረግ፣

### 1.1 ለማገዶ፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለአካባቢ እንክብካቤና ለሌሎች ጥቅሞች የሚዉል ደን በግለሰቦች፣በማኅበራትና በድርጅቶች እንዲለማ ይደረጋል።

### ስትራቴጂዎች

ሀ. ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማኅበራት ዛፍ ለመትከልና የተለያዩ የደን ውጤቶች ለማምረት እንዲችሉ ለደን ልማት ተብለው ከተከለሉና ከሚከለሉ የገጠር መሬቶች የመጠቀም መብት ባለው የክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሠረት እንደሁኔታው ከሊዝ ነፃ እንዲሰጣቸው ማድረግ፣

ለ. በደን ልማት የተሰማሩ ባለሃብቶች፣ማኅበራትና ድርጅቶች በደን ልማት ዘርፍ በዘላቂነት መቀጠል እንዲችሉ የደን ልማት ለተካሄደበት መሬት ደኑ

-----------------------------------------------------------------------------------------------

ለምርት እስኪደርስ ድረስ እንደሁኔታው ከማንኛውም ዓመታዊ የመሬት ግብር ነፃ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

ሐ. ግለሰቦች፣ ማሕበራትና ድርጅቶች ደን ለማልማት ለሚያደርጉት ጥረት አስፈላጊውን ሙያዊ የቴክኒክ ድጋፍ  መስጠት፤

መ. በመንግሥት ይዞታ ሥር ባሉ ምርት ሰጪ ደኖች ውስጥ በግለሰቦች፣ማኅበራትና ድርጅቶች በኮንሴሽን     ሊለሙ የሚችሉ የደን ቦታዎች ለሰው ሰራሽ ደን ልማት ተለይተው እንዲዘጋጁ ማድረግ፤

ሠ. ግለሰቦች፣ ማሕበራት ወይም ድርጅቶች ለአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ለሚያደርጉት የደን ተከላ ሥራ የሚሆን ዘር/ችግኝ ከመንግሥት እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ረ. በደን ልማትና በደን ነክ ኢንዱስትሪ ላይ ለሚሰማሩ ግለሰቦች የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

ሰ. ግለሰቦች በደን ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው የኢንቨስትመንት አማራጮችና  የደን መሬቶች በጥናት እንዲለዩና እንዲታወቁ ማድረግ፣

ሸ. በጥምር ግብርናና ደን አመራረት ዘዴ ከፊል የእርሻ መሬታቸውን ለዚህ ተግባር  ለሚያውሉ አርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች በጥምር ደኑ ተክል ከተያዘው የመሬት ስፋት መጠን አኳያ የመሬት ግብር ክፍያ ቅናሽ የሚያገኙበትን  ሁኔታ ማመቻቸት፣

**1.2 ማንኛውም ግለሰብ፣ ማኅበርና ድርጅት በይዞታው በሚገኝ፣ ወይም በኮንሴሽን ተከልሎ በሚሰጠው የመንግሥት ደን ውስጥ በሚያለማው ደን የሚኖረው የባለቤትነት ዋስትና የተረጋገጠ እንዲሆን ይደረጋል።**

## ስትራቴጂዎች

ሀ. በመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ደንብና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሚወጡት ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች መሠረት በግለሰብ፣ በማኅበራትና በድርጅት ለሚለሙ የደን መሬቶች የይዞታ ዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጥ ማድረግ፣

ለ. የደን ባለይዞታዎች በመሬት የመጠቀምና ይዞታዉን የማስተላለፍ መብቶችም በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ መሠረት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣

ሐ. በደን ልማት በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ግለሰብ፣ማኅበርና ድርጅት መሬቱን ለተባለው ዓላማ ማዋሉንና በማኔጅሜንት ፕላን መሠረት መተግበሩን በየጊዜው አግባብ ባለው አካል ክትትልና ግምገማ ማድረግ፣

## 2. የደን ልማት ቴክኖሎጂ ስለማስፋፋት

### 2.1 የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ በመጠቀም የደን ልማት በሀገሪቱ በስፋት እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## ስትራቴጂዎች

ሀ. በተለያዩ የግብርና ሥነ-ምሕዳር ቀጣናዎች ተስማሚነት ያላቸዉ የደን ቴክኖሎጂዎች በምርምር እየበለፀጉ ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱና በጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማድረግ፣

ለ. እንደየግብርና ሥርዓተ-ምህዳሩ ለተጠቃሚዎች የተሠራጩትን የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ቴክኖሎጂዎችን በየጊዜዉ ተጠቃሚ ኅብረተሰቡን በማስገምገም ማሻሻል፣

ሐ. በተለያዩ የግብርና ሥነ - ምሕዳር ቀጠናዎች ተስማሚ የሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ የደን ዝርያዎች የዘር አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፣

መ. ለደን ኢንዱስትሪ ልማት ተስማሚነት ያላቸውን የደን ዝርያዎች በጥናትና በምርምር ከአገር ውስጥና ከውጭ በማሳባሰብ፣ በመምረጥና በማላመድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ሠ. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውና በመጥፋት ላይ ላሉ ለሀገራችን የደን ዝርያዎች ቅድሚያ በመስጠት የአበቃቀላቸውንና የአስተዳደጋቸውን ባህርይ እንዲሁም ስለጥበቃቸው፣ ልማታቸውና ስለአጠቃቀማቸው ተከታታይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣

ረ. የጥምር እርሻና ደን ዘዴ በይበልጥ በኅብረተሰቡ ዘንድ እንዲሠርፅ ለማድረግ የሙያ/ቴክኒክ፣ የዕፅዋት ዘርና ችግኝ ማግኛና ማትጊያ ዘዴ በመንደፍ በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ፣

ሰ. ተስማሚነት/አዋጭነት ባላቸው የደን ዝርያዎች ላይ የግብርና ሥነ-ምኅዳር ቀጣናን መሠረት ያደረጉ ጥናቶችንና ምርምሮችን በማካሄድ ዉጤታማ የሆኑትን በመለየት ለተጠቃሚ ክፍሎች ማድረስ፣

ሸ. ለግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ እድገት እገዛ የሚያደርጉ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውን ሁለገብ ዛፎች በጥምር እርሻ ደን ልማት ማስፋፋት፣

ቀ. አርሶአደሩ/ከፊል አርብቶ አደሩ ምጉዞታው ሥር ያለውን የእርሻ መሬት ከአፈር መሸርሸር ለመጠበቅና ለይዞታው ወሰን/ድንበር አገልግሎት የሚሆን የዛፍና የመኖ ዕፅዋት ዝርያዎችን በመምረጥ እንዲተከል ማድረግ፣ ያሉትንም እንዲንከባከብ የሙያ ዕገዛ መስጠት፣

በ. ደን በአግባቡ እንዲለማ፣ እንዲጠበቅና ጥቅም ላይ እንዲውል በደን ልማት ለተሰማሩ ሁሉ ዘመናዊ የደን ልማት ማኔጅመንት እውቀት እንዲኖራቸው ሥልጠናና ትምህርት መስጠት፣

ተ. በደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ያሉትን ሀገር በቀልና የውጭ እውቀቶች፣ ልምዶችና ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት የደን አልሚውን እውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣

ቸ. ለአርሶ አደሩ/ለከፊል አርብቶ አደሩና ለግል ባለሃብቱ የሚቀርቡ የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆችና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ገቢን ለማሳደግና በአጭር ጊዜ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ አስተወጽኦ ያለው በመሆኑ የሚደረጉት ጥረቶች በዚህ ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑ ማድረግ፣

ነ. የደን መመናመንን ለመቀነስና በዘላቂነት ለተሻለ አገልግሎት እንዲውል ለማገዶ ፍጆታ የሚሆን አማራጭ የኃይል ምንጮችን ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ እንዲደርስ አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር/በቅንጅት መሥራት፣

## 3. <u>የደን ገበያ ልማት ስለማስፋፋት</u>

### 3.1 አርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች፣ ባለሀብቶች፣ ማህበራት፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የንግድ ድርጅቶችና ተቋማት ደረጃቸውን የጠበቁና ለገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የደንና የደን ውጤቶችን በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ፡፡

## <u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. የዛፍ ችግኝ በማፍላትና በማዘጋጀት ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ ለመሸጥ ለሚሰማሩ አካላት እገዛ ማድረግ፣

ለ. በደን ማኔጅመንት ፕላን መሠረት የደን ምርት ለንግድና ለኢንዱስትሪ ልማት እንዲውል ማድረግ፤

ሐ. ለደንና ለደን ውጤቶች ንግድ የሚሰጠው ፈቃድ የሀገሪቱን ውስን የደን ሀብት ዘለቄታዊ አጠቃቀም በአገናዘበና የአከባቢውን የተፈጥሮ ሀብት መዛባት በማያስከትል መንገድ በሚዘጋጅ የማኔጅመንት ዕቅድ መሰረት እንዲሆን ማድረግ፣

መ. ለገበያ ተፈላጊ ለሆኑ ዛፎች ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣

ሠ. ለደን ልማት ተስማሚ በሆኑ የግብርና ሥነ-ምሕዳር ቀጣናዎች ለሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች በደን ልማት፣ ጥበቃና ግብይት ላይ ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ሥልጠና መስጠት፣

ረ. ባለሀብቶች በደን ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ የሚያስችሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ማበረታቻዎችን ማመቻቸት፣

## 3.2 በአገር ውስጥና በውጪ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ የደን ውጤቶች የሚያስገኙ ደኖች ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ምርቱ በጥራትና በብዛት እየተመረተ ለገበያ እንዲቀርብ ይደረጋል::

## <u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. በደኑ አካባቢ የሚኖረው አርሶ አደር /ከፊል አርብቶ አደር በማኅበር/በቡድን እንዲደራጅ በማድረግ  የማምረቻ ቦታ ተከልሎ እንዲሰጥ ማድረግ፣

ለ. ስለደኑ እንክብካቤና አያያዝ እንዲሁም ስለደንና የደን ውጤቶች አመራረት የተግባር መመሪያ ማዘጋጀትና ሥልጠናና  ትምህርት መስጠት፣

ሐ. ጥራት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ ምርት በማዘጋጀት ለገበያ እንዲቀርብ ድጋፍ ማድረግ፣

መ. በደኑ አካባቢ ከሚኖረው ሕብረተሰብ ጎን ለጎን የግል ድርጅቶችና ባለሀብቶች የሰው ኃይል በማሰማራት የደን ውጤቶችን  በጥራትና በብዛት

እያስመረቱ ለአገር ውስጥ ገበያ እንዲሁም በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ ምርት እንዲያቀርቡ ማበረታታትና የሙያ ድጋፍ መስጠት፣

ሠ. ከዛፍ የሚሰሩ ቁሳቁሶችን አዘጋጅተው ለገበያ ለሚያቀርቡ አርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች የሙያ ሥልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

## 4. <u>የመንግሥት ደን አስተዳደርና ማኔጅመንት</u>

### 4.1 በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የመንግሥት ደንና የደን መሬቶች በጥብቅ ደንነትና በምርት ሰጪ ደንነት በሁለት ምድብ ተለይተው በሚዘጋጅላቸው የማኔጅመንት ፕላን መሠረት እንዲተዳደሩ ይደረጋል፡፡

### <u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. ትኩረት የተሰጣቸውና በክልል መንግሥታት ሥር የሚተዳደሩ የመንግሥት ደኖች በሚዘጋጅላቸው መስፈርት መሠረት በምርት ሰጪነትና በጥብቅ ደንነት ተለይተው ዘላቂ ምርታማነታቸው ሳይቀንስ እንዲለሙና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ለ. ለመንግሥት ደኖች የአስተዳደርና የማኔጅሜንት ፕላን በማዘጋጀት ለተፈለገው ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ፣

**4.2 በጥብቅ ደንነት የሚከለሉ ደኖችና የደን መሬቶች በተለይም ሊጠፉ የተቃረቡ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች ክምችት ያለባቸው ደኖች ዳር ድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሰረት ዕውቅና እንዲያገኙ በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥታት እንዲተዳደሩና ጥቅም እንዲሰጡ ይደረጋል።**

## ስትራቴጂዎች

ሀ. ጥናቶችን መሠረት በማድረግ የጥብቅ ደኖች ስፋት፣ አቀማመጥና የደን ዕፅዋት ስብጥር ለይቶ መረጃ በማሰባሰብና በማጠናቀር ሕብረተሰቡን ያሳተፈና የብዝሐ ሕይወት ጥበቃንና አጠቃቀምን ግምት ውስጥ ያስገባ የደን ማኔጅሜንት ፕላን ማዘጋጀት፣

ለ. በአግባቡ ባለመከለላቸውና ባለመጠበቃቸው ምክንያት አፈራቸው በነፋስና በዝናብ ተጠርጎ ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡና የሚጋለጡ ቦታዎችንና የውሃ አካሎችን ለመጠበቅና ለማሻሻል እንዲሁም ተፋሰሶችን በአግባቡ ሊጠብቁ የሚችሉ ደኖችና የደን መሬቶች እንዲሆኑ በጥብቅ ደንነት ተከልለው እንዲጠበቁ በማድረግ እንደሁኔታው በአካባቢው ሕብረተሰብ ተሳትፎ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን የማኔጅመንት ሥልት መንደፍና ተግባራዊ ማድረግ፣

ሐ. በጥብቅ ደኖች ዙሪያ የደኑን ዳር ድንበር የሚያመላክቱና ለአካባቢው ሕብረተሰብ ለማገዶና ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ፈጣን እድገት ያላቸው የዛፍ ዝርያዎች እንዲለሙ ማድረግ፣

መ. ጥብቅ የመንግሥት ደኖች ውስጥ የሚገኙ ሊጠፉ የተቃረቡ የዕፅዋት ዝርያዎች ከማንኛውም የምርት ሥራ እንቅስቃሴ ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ:: ሆኖም ዕድሜያቸውን የጨረሱ ዛፎች በደኑ ውስጥ ብዙ በመቆየት በቀላሉ በበሽታ በመጠቃት ቀሪውን ደን የሚጎዱ መሆኑ ከተረጋገጠ ዛፎቹን በመቁረጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ሠ. በጥብቅ ደን አካባቢ፣ በደኑ ውስጥና ዙሪያ ለሚኖሩ አርሶ አደሮች/ከፊል አርብቶ አደሮች አሳታፊ የደን ልማትና አጠባበቅ ትምህርት በመስጠት፣በንብ ርባታ፣ በቅመማ ቅመምና በጫካ ቡና ማምረት፣ በእንስሳት መኖ ምርት ወዘተ እንዲጠቀሙ ፈቃድና ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት ማበረታታት፣

## 4.3 ምርት ሰጪ ደኖች ተለይተው ዳር ድንበራቸውን በመከለልና ሕጋዊ እውቅና በመስጠት አግባባ ባለው መንግሥታዊ አካል ወይንም በግል /በማህበራት እንዲተዳደሩ ይደረጋል::

### <u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. በእያንዳንዱ ምርት ሰጪ የመንግሥት ደን ክልል ያለውን የዛፍ ዓይነት፣ ክምችትና የምርት መጠን በማጥናት በደን ውስጥ ምን ያህል የግንድ

ክምችት እንዳለ፣ ስንት ዓይነት የዛፍ ዓይነቶች እንዳሉ፣ የደኑ ስፋትና የደኑ ራሱን የመተካት ባሕርይ፣ ከደኑ ውስጥ በየዓመቱ ሊገኝ የሚችለውን የምርት መጠንና ለስንት ዓመት በምርት ሰጪነት እንደሚያገለግል መረጃዎችን በማሰባሰብ በአካባቢው ሕብረተሰብ ተሳትፎ የማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት ተግባራዊነቱን መከታተል፣

ለ. ለሀገር ውስጥ ገበያም ሆነ ለውጭ ገበያ በቂና አስተማማኝ የደን ሀብት ውጤት ለማምረት እንዲቻል ልማቱ እንደአስፈላጊነቱ በመንግሥት፣ በግል፣ በመንግሥትና በግል /በሽርክና/በኮንሴሽን ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚወጣላቸው የማኔጅመንት ፕላን መሠረት እንዲካሄድ ማድረግ፣

ሐ. በሰው ሰራሽ መንገድ የለሙና የሚለሙ ደኖች በተለይ ፈጣን እድገትና ወጥነት ያለው ግንድ ያላቸው የዛፍ ዝርያዎች በአብዛኛው የማገዶ፣ የግንባታና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ፍላጎትን እንዲያሟሉ ልማቱን ማፋጠን፣

## 4.4 በጥብቅ ወይም በምርት ሰጪ ደንነት ያልተያዙና ያልተከለሉ ተበታትነው የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖች በዘፈቀደ ለኮንስትራክሽን፣ ለማገዶና ከሰል ምርት ጥቅም ላይ እንዳይውሉና የአካባቢ የተፈጥሮ ሁኔታ መናጋት እንዳያስከትሉ ደኖቹን በቀበሌ አስተዳደር ወይም በግለሰቦች የይዞታ ባለቤትነት

እንዲያዙና በሚወጣላቸው የአጠቃቀም እቅድ መሠረት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

## ስትራቴጂዎች

ሀ. በመንግሥት ጥብቅና ምርት ስጪ ደን ተብለው ያልተለዩትን/ያልተከለሉትን የተፈጥሮ ደኖች በጥናት በመለየት በጥብቅ ወይም በምርት ሰጪ ደን በመከፋፈል ጥቅም ላይ ማዋል፣

ለ. በጥብቅ ወይም በምርት ሰጪነት ያልተከለሉ የተፈጥሮ ደኖችን ከአከባቢው ሕብረተሰብ ጋር በመሆን የማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት አልምተው ለሚጠቀሙ ለአከባቢው ነዋሪዎች፣ ግለሰቦች፣ ማህበራት ወይም ባለሀብቶች በሚወጣ መመሪያ መሠረት ጠብቀውና አልምተው እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

ሐ. ያልተከለሉ የተፈጥሮ ደኖችንና የደን መሬቶችን በመሬት አጠቃቀም ፕላን መሠረት በመከለል የደን ልማት እንዲስፋፋባቸው ማድረግ፣

# 5. የደን ሀብትን ከልዩ ልዩ ጥፋቶች መከላከል

5.1 በማንኛዉም ይዞታ ሥር የሚገኝ ደን ከተፈጥሮም ሆነ ሰዉ ሰራሽ አደጋዎች ጥፋት እንዲጠበቅ በማድረግ ለደን ጥፋት መፍትሄ የሆኑ ተግባራት ሁሉ እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡

# ስትራቴጂዎች

ሀ. ትኩረት በተሰጣቸው የመንግሥት ደኖች ውስጥ የደን ቃጠሎ፣ ያለፍቃድ በደን ውስጥ መስፈር፣ ለተለያየ ዓላማ የደን ምንጣሮና የመሳሰሉት ተግባራት እንዳይካሄዱ ለመከላከል በአከባቢው ህብረተሰብና በሚቀጠሩ የደን ዘቦች ጥበቃ ማድረግ፣

ለ. ኅብረተሰቡ በደን ጥበቃ ሥራ ላይ እንዲሳተፍና የደን ምንጣሮንና ጭፍጨፋን እንዲከላከል አስፈላጊው ትምህርትና ተቋማዊ ድጋፍ እንዲሰጠውና ተሳትፎውም በዘላቂነት እንዲጎለብት ማድረግ፣

ሐ. በተፈጥሮ ባህሪያቸው የደን እሳት መከላከል የሚችሉ የዕፅዋት ዓይነቶች በመንግስት ደን ዙሪያ በሁለትና በሦስት ረድፍ በአካባቢው ህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲተከሉና ከምርቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

መ. በደን ሀብት ላይ በተለያየ መንገድ ጥፋት የሚያደርሱ ሁሉ ለሕግ ቀርበው ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ሠ. ሀገራችን የአካባቢ ጥበቃን አስመልክቶ የፈረመቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን (እንደ ብዝሐ ሕይወት ጥበቃና በረሀማነት መስፋፋትን መከላከል፣ ረግረጋማ ቦታዎችን መጠበቅ) ተግባራዊ ማድረግ፣

ረ. በመንግሥትና በግል ደኖች ውስጥ የተለያዩ ተዛማች በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና መከታተል፣

## 5.2 ዝርያቸው በመጥፋት ላይ በሚገኙ የደን ዕፅዋት ዘረመል ዝውውር ላይ ጥበቃና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

## ስትራቴጂዎች

ሀ. በመጥፋት ላይ የሚገኙ የደን ዕፅዋት ዝርያዎች ዝውውር ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦችና መመሪያዎች ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፣

ለ. የደን ሀብትን ለመጠበቅ አግባብ ያለው ተቋም ከሌሎች አግባብ ካላቸው ድርጅቶች ማለትም ከጉምሩክ፣ ከቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ከፖሊስ፣ ከቀበሌ አስተዳደርና ከአካባቢው ሕብረተሰብ ጋር ቅንጅት በመፍጠር የቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፣

ሐ. የጄኔቲክ ሀብት ጥበቃን ለማጠናከር እንዲቻል ትኩረት በተሰጣቸው የመንግሥት ደኖች ባሉበት ተፈጥሮአዊ ክልል የዘቦታና በሳይንሳዊ ዘዴ በማራባት የኢዘቦታ ማንበር መጠቀም፣ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ የደን ዕፅዋት ዝርያዎች ከሀገር እንዳይጠፉ ጥበቃ ማድረግ፣

መ. በመጥፋት ላይ ያሉ የደን ዕፅዋት ዝርያዎች ላይ የሚደረገው ጥበቃ ዓለም አቀፍ የንግድና የብዝሀ ሕይወት ሕግ ስምምነትን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ፣

## 5.3 የደን ሀብት ዉጤቶችን ዝውውር ለመቆጣጠር የሚያስችል አግባብ ያለው የቁጥጥር ሥርዓት ይቀረፃል፡፡

## ስትራቴጂዎች

ሀ. በመንግሥት ደኖች በደኑ መግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የደን ሀብት መቆጣጠሪያ ኬላ ይቋቋማል፡፡

ለ. አግባብ ያላቸው መ/ቤቶችና ተቋማት የደንና የደን ውጤቶች ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ ሲወጡና ከውጭ ወደ ሀገር ሲገቡ በሚደረገው ቁጥጥር አስፈላጊውን ትብብር/ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

ሐ. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የደን የደን ውጤቶች ደረጃቸውን የጠበቁና ከተለያዩ ተላላፊ  በሽታዎች የፀዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥና ዝውውሩም በሕጋዊ መንገድ መሆኑን ቁጥጥር ማድረግ፣

መ. በየደረጃው የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና ማሕበራት በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ በሕገወጥ የደን ሀብት ዝውውር ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

ሠ. ሕገወጥ የደንና የደን ውጤቶች ዝውውርን በዘላቂነት ለመግታት የሚያስችል ሕግ በሕብረተሰቡ ተሳትፎ በማዘጋጀት በሥራ ላይ ማዋል፣

# 6. በደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት ስለመዘርጋት

**6.1 በደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ያተኮረ ወቅታዊ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ፣ቅንብርና ሥርጭት ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ በየደረጃው እንዲዘረጋና ተገቢውን አገልግሎት እንዲያበረክት ይደረጋል።**

## ስትራቴጂዎች

ሀ. በግል፣ በማህበርና በባለሀብቶች የተያዘ የደን የይዞታ መጠንና የአጠቃቀም ሁኔታን በተመለከተ መረጃዎችን በማሰባሰብ በአግባቡ እንዲያዝ ማድረግ፣

ለ. የደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ስትራቴጂዎችን ለመተግበር የሚረዱ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣በማደራጀትና በመተንተን ለሕብረተሰቡ በወቅቱ እንዲሰራጩ ማድረግ፣

ሐ. ባህላዊና ዘመናዊ ጥምር የእርሻና ደን ዘዴዎች ላይ ጥናት በማካሄድ ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ እንዲደርሱ ማድረግና በየጊዜው መገምገምና ማሻሻል፣

መ. በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ገበያ ተፈላጊ የሆኑ የደንና የደን ውጤቶች ዓይነቶችን በመለየትና የገበያ ዋጋ ጥናት መረጃ ተሰብስቦና ተጠናቅሮ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ማድረግ፣

ሰ. በደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም፣በመረጃ አሰባሰብ፣ በደን ማኔጅመንት ኘላን ዝግጅትና ሌሎች አስፈላጊ የሙያ መስኮችን በመለየት የአጭርና የረዥም ጊዜ የሥልጠና ኘሮግራም በመንደፍ ለባለሙያዎች እንዲሰጡ ማድረግ፣

## 6.2 የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ ልውውጥና ቅብብሎሽ በሀገር ውስጥና በዓለም ዓቀፍ የመረጃ መረብ ቅንጅትና ትስስር ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

## <u>ስትራቴጂዎች</u>

ሀ. በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚወጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና የዳበሩ የአሠራር ልምዶች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንዲሰባሰቡ ማድረግ፣

ለ. የመረጃ ልውውጥና ቅብብሎሽ ቅንጅትና ትስስር ዘላቂነት እንዲኖረው የሚያስችሉ ደረጃቸውን የጠበቁና ወጥ የመረጃ ልውውጥ ቅጾች ወይም ፎርማቶች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

ሐ. በሀገር ውስጥ በየደረጃው የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የሚያቀብሉና አቀነባብረው የሚያሰራጩ አካላት በሰው ኃይልና በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና መሣሪያ እንዲጠናከሩ ማድረግ፣

መ. የአካባቢ የተፈጥሮ ሚዛን እንዳይዛባ በተለያዩ ሥነ-ምሕዳር ቀጣናዎች የሚገኘው የተፈጥሮ ደን ያለ አግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ሕብረተሰቡን ማስተማር፣